Maryland's Largest School District

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

# በአስተማማኝነት የሚጠበቅ በሂደት ላይ ያለ መረጃ፡-

## 1973 የተሐድሶ ደንብ ሰክሽን 504/Section 504 of the Rehabilitation Act of 1973

የሚከተለው አጭር መግለጫ በፌደራል ህግ እና በሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የተሰጡ መብቶችን የሚመለከት ነው (MCPS) Regulation ACG-RB፣የ1973 ሰክሽን 504 የመልሶ ማቋቋም ደምብ መሠረት ብቃት ላላቸው/ ለሚታቀፉ ተማሪዎች ተገቢ የሆኑ መገልገያዎች/Accommodations እና ማሻሻያዎች ፣ 1973 ሰክሽን 504 የመልሶ ማቋቋም ደምብ መሠረት ስንክልና ያላቸውና ሰክሽን 504 ለመታቀፍና መገልገያዎችን/Accommodations ድጋፍ ለማግኘት ብቃት ላላቸው ተማሪዎች።

### በሰክሽን 504 መሠረት የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል/ይኖሯታል

1. የእርስዎ ተማሪ ተሳታፊ የመሆን እና በአካል ስንክልና ምክንያት ምንም አይነት አድሎ ሳይደረግበት/ሳይደረግባት ከህዝባዊ የትምህርት መርሀግብሮች ጥቅማጥቅሞችን ይቀበላል/ትቀበላለች።
2. ስለ ተማሪዎ መለያ፣ ግምገማ፣ ዳግም ግምገማ፣ ወይም የምደባ/የፕሮግራም ውሳኔዎችን በተመለከተ ማሳወቂያ ይደርሰዋል/ይደርሳታል።
3. ልጅዎ አግባብነት ያለውን ህዝባዊ ትምህርት በነፃ ያገኛል/ታገኛለች። ይህም በተቻለ መጠን የአካል ስንክልና ከሌለባቸው ተማሪዎች ጋር አብሮ የመማር መብትን ያካትታል።
4. የእርስዎ ተማሪ ማግኘት ያለበትን/ያለባትን እድሎች የአካል ስንክልና ከሌለባቸው ተማሪዎች ጋር እኩል በት/ቤት ፕሮግራሞች ላይ የመሳተፍ፣ እና በትምህርት ቤት ስፖንሰር በሚደረጉ ከካሪኩለም ውጭ በሚሰጡ እንቅሥቃሴዎች ሁሉ ላይ የመሳተፍ እድል ይኖራል።
5. መለያ መታወቂያ፣ ግምገማ፣ እና የምደባ/ፕሮግራም የተደረጉ ውሳኔዎች፣ ከተለያዩ ምንጮች በሚገኙ መረጃዎች/ ኢንፎርሜሽን ተመስርቶ እና የተማሪውን ፍላጎት ከሚያውቁ ሰዎች፣ የግምገማው ትርጉም፣ እና የምደባ/ፕሮግራም አማራጮችን ያካትታል።
6. በህጉ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ-MCPS ደንብ JOA-RA መሠረት የተማሪ ሪኮርድ የተማሪዎን የትምህርት ሪከርዶች ይመርምሩ እና የራስዎን ቅጂ ያግኙ።
7. የጉዳዮችን መፍትሔ/ውሳኔ የማግኘት ስለእርስዎ ተማሪ የማንነት ማረጋገጫ፣ ስለ ግምገማ፣ ዳግመኛ ግምገማ ወይም የምደባ/ፕሮግራም።

- ሰክሽን 504 በአስተዳደራዊ ግምገማ እንዲታይ ለመጠየቅ MCPS የልዩ ትምህርት ጽ/ቤት፣ የቅሬታና ውሳኔ ሰጪ ክፍል አማካይነት የሰክሽን 504 አስተባባሪን ማግኘት ይችላሉ።
- MCPS ሰክሽን 504 አስተባባሪን በማግኘት በሜሪላንድ አስተዳደራዊ ጽ/ቤት አማካይነት የግልግል ዳኝነት እንዲታይ ለመጠየቅ ይቻላል። በግልግል ሁኔታ ወላጆችን/ሞግዚቶችን የስምምነት ድርድር በማድረግ ንቁ ተሳታፊ/ፓርትነር እንዲሆኑ ይረዳል።
- MCPS ሰክሽን 504 አስተባባሪን በማነጋገር በሜሪላንድ የአስተዳደር ቢሮ በኩል የሰክሽን 504 በችሎት እንዲታይ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። ችሎቱ በአስተዳደራዊ ህግ ዳኛ ይመራል/ይካሄዳል። ችሎቱ ወላጆች/ሞግዚቶች እንዲሳተፉ እና በካውንስል የመወከል እድል ይሰጣቸዋል። ከሁለቱ አንዳቸው የይግባኝ ሰሚ ባለስልጣኑን ውሳኔ ይግባኝ ለመጠየቅና እና ውሳኔው እንዲገመገም ሊጠይቁ ይችላሉ
- በተጨማሪም፣ ዩ. ኤስ. የትምህርት ዲፓርትመንት የዜጎች መብት ጽ/ቤትን በስልክ ቁጥር 215-656-8541 ለመገናኘት ይቻላል።


MCPS ሰክሽን 504 የማስፈጸም ሃላፊነት ያለው ሰው፡-
MCPS ሰክሽን 504 አስተባባሪ
Resolution and Compliance Unit
850 Hungerford Drive, Room 208
Rockville, MD 20850
ስልክ:- 240-740-3230
TDD/TTY: 301-279-312